# የድረሱልኝ ጩኸት

የተወደዳችሁ የእግዚአብሔር ልጆች እስኪ ሳነብብ ካገኝሁት ሳካፍሳችሁ ብዬ ከዚህ ቀጥሎ የምታነብቧትን ጽሑፍ ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ መልሼ የራሴንም ሐሳብ አክየባት ጣፍኋት። አንብበን ቁም ነገሯን እናስተውል።

አቶ ፍቅር፣ አቶ ሀብት፣ ወይዘሮ ከንቱ ውዳሴ፣ አቶ ሐዘን፣ ወይዘሮ ደስታ፣ አቶ ተስፋ፣ ወይዘሮ እምነት እና ሌሎችም በአንዲት ደሴት ይኖሩ ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን ደሴቲቱ የመስመጥ አደጋ እንደሚደርስባት ታውቆ ሁሉም ነዋሪዎች ጀልባዎቻቸውን አዘጋጅተው በፍጥነት እንዲለቁ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ታወጀ። አብዛኛዎቹ ነዋሪዎች ጀልባዎች ነበሯቸው። ከነዋሪዎቹ ሁሉ አቶ ፍቅር ጀልባ አልነበረውም፤አቶ ፍቅር በባህርይው ቶሎ የማይደነግጥ፣ አንድን ነገር እስከ መጨረሻው ሳያደርስ የማይለቅ ነው። ‘ፍቅር እስከ መቃብር’ እንዲሉ። በመሆኑም የደሴቲቱን የመጨረሻ እጣ ፋንታ ለማየት ጸንቶ ቆየ።

ጉዞው ቀጠለ። ሩጫ ሽብር፣ እግሬ አውጭኝ እኔ አመልጥ እኔ አመልጥ ትንቅንቅ ተጀመረ ፤ የሌለው ሰው በእንዲህ ዓይነት ጊዜ ካለው እገዛ መጠየቅ ግድ ነውና ደሴቲቱ መስመጥ ስትጀምር አቶ ፍቅር እርዳታ ለመጠየቅ ወሰነ። አቶ ሀብት በሚያምር ትልቅ ጀልባ ተጭኖ እየተንዘ እያለ አቶ ፍቅር “አቶ ሀብት በጀልባህ ልታሳፍረኝ ትችላለህ?” ብሎ ሲጠይቅ አቶ ሀብት “የለም አልችልም ብዙ ወርቅ እና ብር ጀልባዬን አጣብቦታል፤ስለዚህ ላንተ ቦታ የለኝም” ብሎ ሲመልስለት አቶ ፍቅር ኩምሽሽ አለ።

‘የሌለው ልብ የለው’ እንዲሉ ሌላው ሲያልፍ እድሉን ለመሞከር ተዘጋጅቶ እንደገና በአጠገቡ ስታልፍ የነበረችው ወይዘሮ ከንቱ ውዳሴን አቶ ፍቅር ጠየቀ፤ እንዲህ ሲል “ወይዘሮ ከንቱ ወዳሴ እባክሽን እርጅኝ በጀልባሽ አሳፍሪኝ” አላት ፤ወይዘሮ ከንቱ ወዳሴም “የለም አቶ ፍቅር እቃህም፣ ልብስህም፣ ሰውነትህም በውሃ ርሷል እና ጀልባዬን ስለምታበላሽብኝ ልረዳህ አልችልም አላሳፍርህም” ብላ እምቢ አሻፈረኝ አለች። አሁንም አቶ ፍቅር አዘነ፤ግን ተስፋ አልቆረጠም።

በመሆኑም አቶ ሐዘን በበኩሉ በአቶ ፍቅር አጠገብ ሲያልፍ አቶ ፍቅር “አቶ ሐዘን እባክህ አብሬህ ልሂድ” ብሎ በመማጸን ጠየቀ። አቶ ሐዘንም “ኦኦ አቶ ፍቅር በጣም አዝናለሁ እኔ ለብቻዬ ነው መሄድ የምፈልገው” በማለት ይመልሳል። አሁንም ተስፋ አልቆረጠምና አቶ ፍቅር በመቀጠል ወይዘሮ ደስታ እንዲሁ ስታልፍ የእርዳታ ጥሪ አሰማ። ነገር ግን ወይዘሮ ደስታ በባህርይዋ ግር ግር የምትወድ በመሆኗ ከደሴቷ መውጣቷ አስደስቷት እንደሆነም አይታወቅም ብቻ በጣም ከመደሰቷ የተነሳ አቶ ፍቅር ሲጣራ እንኳ ሳትሰማው አለፈች።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ድንገት እንዲህ የሚል ድምጽ አቶ ፍቅር ሰማ "አቶ ፍቅር! አይዞህ! ና እኔ እወስድሃለሁ ተሳፈር" የሚል የምሥራች አዋጅ፤ ተናጋሪዋ አንድ በእድሜዋ ጠና ያለች ሴት ነበረች።አቶ ፍቅርም በጣም ደስ ብሎት ተሳፈረና በሰላም ከተሻገሩ በኋላ ወይዘሮዋ ለአቶ ፍቅር መልካም ተመኝታለት መንገዷን ቀጠለች ። በመሃሉ አቶ ፍቅር ያች ሴት ያደረገችለት ውለታ ትልቅ በመሆኑ ውስጡን ናጠውና ስሟን እንኳ ሳይጠይቅ መቅረቱ ከንክኖት አንድ በእድሜው በሰል ያለና በቅርብ የሚያውቀው አቶ ተስፋን ጠጋ ብሎ "ይህች ከዚያ ጭንቅ ያወጣችኝ ሴት ስሟን ልትነግረኝ ትችላለህ?" ብሎ ይጠይቃል።

አቶ ተስፋም ፈገግ አለና "ወይዘሮ እምነት ትባላለች" ሲለው አቶ ፍቅርም "እምነት? ወይዘሮ እምነት እንዴት እጅግ ድንቅ ሴት ናት በማለት አድንቆ ከባድ ውለታ ነው የጣለችብኝ እንዴት ውለታውን እንደምመልስ እንጃ!" ሲል አቶ ተስፋ ፈገግ አለና "አቶ ፍቅር፣ ምንም አያሳስብህ ወይዘሮ እምነት ካንተ ምንም የምትፈልግ አይደለችም ይህን ያደረገችው ታላቅነትህን ስለተረዳች ብቻ ነው" ሲል የወይዘሮ እምነት አስተዋይነትን በውል አስገነዘበው ። ለነገሩ አቶ ፍቅር አይገንዘብ እንጅ አቶ ተስፋ በችግሩ ሁሉ በሐሳብ አብሮት ይንቆራጠጥ ነበር፤ የሚገርመው ነገር ወይዘሮ እምነት አቶ ፍቅርን ባሳፈረችባት ጀልባ ለአቶ ፍቅር ባይታየውም አቶ ተስፋ አብሮ ነበር።




'A Cry for Help' ከተባለና ደራሲው ካልታወቀ እንግሊዝኛ መጣጥፍ ተተረጎመ።

በመ. ደምለው ደነሱ

ኦስሎ

<u>ማሳሰቢያ</u>

ደራሲው ያልጨመራቸውን ግን ያመቻሉ ብዬ የገመትኳቸውን ነጥቦች አካትቻለሁ፤እንዲሁም ደራሲው የጨመራቸውን ግን አይመቹም ያልኳቸውን ነጥቦችም አስቀርቻለሁ።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር